15

አፍሪካ ቲቪ

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# سُورَةُ التِّينِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

وَٱلتِّينِ وَٱلزَّيۡتُونِ ١ وَطُورِ سِينِينَ ٢ وَهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ٱلۡأَمِينِ ٣
لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِيٓ أَحۡسَنِ تَقۡوِيمٖ ٤ ثُمَّ رَدَدۡنَٰهُ أَسۡفَلَ سَٰفِلِينَ
٥ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَلَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ مَمۡنُونٖ ٦
فَمَا يُكَذِّبُكَ بَعۡدُ بِٱلدِّينِ ٧ أَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِأَحۡكَمِ ٱلۡحَٰكِمِينَ ٨

# ሱረቱ አት-ቲን

- (የበለስ ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የአናቅፁ ብዛት (8) ናቸው፡፡
- ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-
- የሠው ልጅ ክብርና ዋጋ የሚኖረው በእምነቱ መሆኑ በአንፃሩ ደግሞ ውርደትና የበታችነት የሚገጥመው እምነቱን ሲተው በመሆኑ አላህ ራዕይ በሚያወርድባቸው ቦታዎች ይምላል።

አፍሪካ አካዳሚ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) አላህ በበለስና በሚያድግበት ቦታ እንዲሁም በዘይቱንና በሚበቅልበት እንዲሁም ዒሳ (ዐለይሂ አሰላም) በተላኩበት ፍልስጤም ምድር ይምላል።
- (2) ነቢዩ ሙሳን (ዐለይሂ  አሰላም) ባናገረበት የሲናይ ተራራም ይምላል።
- (3) በተቀደሰው አገር በውስጡ የገባ ሰላም በሚያገኝበት እንዲሁም ሙሐመድ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በተላኩበት በመካ ይምላል።
- (በበለስና፤ በዘይቱን ዛፍ፤ በሲና ተራራና፤ በዚህ በፀጥተኛው (ፀጥታ በነገሰበት) አገር በመካ እምላለሁ፡፡)

- (4) በእርግጥም የሰውን ልጅ የተስተካከለ ቁመና በአማረ አቋም የተሻለ ቅርፅ ያለው አድርገን ፈጠርነው።
- (5) በመቀጠልም በዱንያ ህይወት ውስጥም ወደ እርጅና እና ወደ መጃጃት እንመልሰዋለን፣ ተፈጥሯዊ እምነቱን ካበላሸና የእሳትም ከሆነ በሰውነቱ እንደማይጠቀመው ሁሉ በሰውነት አካሉ እንዳይጠቀም ይሆናል።

- (6) ግና እነዚያ በአላህ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩት ምንም ቢያረጁ እንኳ ራሳቸውን በማፅዳታቸው የተነሳ የማያቋረጥ ቋሚ ምንዳ ተዘጋጅቶላቸዋል እርሱም ጀነት።
- (7) አንተ የሰው ልጅ ሆይ! የአላህን ታላቅነትን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶችን ከተመለከትክ በኋላ
- ለመሆኑ የፍርዱን ቀን ለማስተባበል ያነሳሳህ ምንድነው?!

- (8) ለመሆኑ አላህ የትንሳኤውን ቀን የምንዳና የፍርድ ቀን በማድረጉ ከዳኞዎች ሁሉ በላጭና ፍትህዊ ዳኛ አይደለምን?!
- በመሆኑም ባሪያዎቹን መልካም ሠሪውን በመልካምነቱ ጥፋተኛውን በጥፋቱ ሳይመነዳና ሳይፈርድ እንዲሁ ይተዋቸዋል ተብሎ ይታሰባልን?!



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ፋቲሓ")

አፍሪካ አካዳሚ

## ከሱረቱ-አት ቲን ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. የዘይቱንና የቲን ዛፎች፤ የሲና ተራራ፤ የመካ አካባቢዎች ያላቸውን ክብር፤
- 2. አላህ የሰውን ልጅ ባማረ ስብዕና በተሻለ ግንባታ በመፍጠሩ የዋለለትን ውለታ ማስታወስ፤
- 3. የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢዋብና ቢያምር ሄዶ ሄዶ ማርጀቱና መጃጀቱ እንደማይቀር፤
- 4. የሰው ልጅ ሲያረጅና ከእንቅስቃሴ ሲቋረጥ በወጣጥነቱ ይሰራው የነበረው መልካም ተግባር ምንዳ እንደሚቀጥልለት፤
- 5. በፍትህ ከአላህ የበለጠ ማንም እንደሌለ እንማራለን፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com